## ዘዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

፲፤ ወሶበሂ ፡ ይፈቅድ ፡ ሕሊና ፡ ይብጻሕ ፡ ኀቤሁ ፡ይደልዎ ፡ ብርሃኑ ፡ እፎኑ ፡ ይክል ፡ ሰብእ ፡ ይነጽር ፡ ፀሐየ ፡ ወይጠይቅ ፡ አምሳሊሁ ፡ እመሰ ፡ ለፍጡራን፡ ኢንክል ፡ ጠይቆቶሙ ፡ እፎኑ ፡ ይትከሀለነ ፡ ጠይቆቶ ለገባሬ ፡ ኵሉ ።

፲፩፤ ወካዕበ ፡ ይመጽእ ፡ ለሊሁ ፡ ዳግመ ፡ በስብሐተ ፡ አቡሁ ፡ በሥጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ በዓቢይ ፡ ግርማ ፡ ወስብሐት ፡ ወይፈድዮ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ። ማቴ፡ ፳፭ ፡ ፴፩ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲ ።

፲፪፤ ወለእለሰ ፡ ይሬስይዎ ፡ ሰብአ ፡ ዕሩቀ ፡ እመለኮት ፡ ወይከፍልዎ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌ ፡ ለሊሁኒ ፡ ይከፍሎሙ ፡ ወይወድዮሙ ፡ ውስተ ፡ ገሃነም ።

፲፫ ፤ ወእለሂ ፡ ይሬስይዎ ፡ ለመለኮት ፡ ሐማሜ ፡ ወድኩመ ፡ ለሊሁኒ ፡ ይጠብሖሙ ፡ በሰይፈ ፡ አፉሁ፡ ዘውእቱ ፡ ቃሉ ፡ በሊህ ፡ ወእለሂ ፡ ያፈልስዎ ፡ እመለኮተ ፡ አቡሁ ፡ ወየሐጽጽዎ ፡እምኔሁ ፡ ውእቱኒ፡ ያሐጽጾሙ ፡ ወያጠፍኦሙ ፡ እመንግሥተ ፡ አቡሁ፡ ቅዱስ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ። ዕብ፡ ፬፡፲፪።

፲፬፤ ወከማሁ ፡ እለ ፡ ያፈልስዎ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ወይሬስይዎ ፡ እምካልእ ፡ አካል ፡ ውእቱኒ፡ ይክልአሙ ፡ ጸጋሁ ፡ ቅዱሰ ።

፲፭፤ ንሕነሰ ፡ ነአምን ፡ ከመዝ ፡ እስመ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ዕሩያን ፡ እሙንቱ ፡ በተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ ወፍጹማን ፡ በ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ዘውእቶሙ ፡ ፩ዱ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ወ፩ዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ ወ፩ዱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

### ምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

፩፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ ዘቍስጥንጥንያ፡ ዘንተ፡ ድርሳነ ፡ ውስተ ፡ ትርጓሜ ፡ መልእክቱ ፡ ለጳውሎስ፡ ሐዋርያ ፡ ብፁዕ ፡ ኀበ ፡ ዕብራውያን ፡ ወውእቱ ፡ ሳብዕ ፡ ድርሳን ፡ እምትርጓሜሁ ።

፪፤ ኢነሥአ ፡ ለዘነሥአ ፡ እመላእክት ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ እምዘርዐ ፡ አብርሃም ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።

፫፤ ኦ ፡ ለዝንቱ ፡ ፍቅር ፡ ዐቢይ ፡ ኦ ፡ ለዝንቱ ፡ ፍቅር ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለትዝምደ ፡ እጓለ ፡ እመ ሕያው ፡ ዘኢይትነገር ፡ ዝንቱ ፡ ዘኢከሠቶ ፡ ለመ ላእክት ።

## ዘዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

፲፤ ልቡናም ፡ መርምሮ ፡ ያውቀው ፡ ቢወድ ፡ ዕውቀቱ ፡ ይደከማል ፡ ሰው ፡ ፀሐይን ፡ ያይ ፡ ዘንድ፡ መልኩንም ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይችላል ? ፍጡራንን፡መርምሮ፡ ማወቅ፡ ካልተቻለን፡ሁሉን፡የፈጠረ ፡ እርሱን፡መርምሮ፡ማወቅ፡እንደ፡ምን፡ይቻለናል

፲፩፤ በክበበ ፡ ትስብእት ፡ ግርማ ፡ መለኮቱን ፤ ጌትነቱን ፡ ገልጦ ፡ በአባቱ ፡ ሥልጣን ፡ ዳግመኛ፡ ይመጣል ፡ ለሁሉም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ይከፍለዋል።ማቴ ፳፭ ፡ ፴፩ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲ ።

፲፪፤ ከመለኮት ፡ የተለየ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሁለት ፡ አካል ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ የሚሉትንም፡ ከምእመናን፡ ይለያቸዋል፡ በገሃነም፡ ይጥላቸዋል ።

፲፫፤ መለኮትን ፡ በባሕርዩ ፡ ታመመ ፡ ደከመ ፡ የሚሉትን ፡ ከአፉ ፡ በሚወጣ ፡ ሰይፍ ፡ ያጠፋቸዋል ፡ ይኸውም ፡ ፈራጅ ፡ ቃሉ ፡ ነው ፡ ከአባቱ ፡ ባሕርይ፡የሚለዩትን ፡ በክብር ፡ በሥልጣንም ፡ ከእርሱ ፡ ያንሳል፡ የሚሉትንም በጌትነቱ ፡ ከሚያወርሳት ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እርሱ ፡ ይለያቸዋል ፤ ያወጣቸዋል፡ ኢሳ ፡ ፲፩፡ ፬ ። ማቴ ፡ ፭፡ ፲፱። ዕብ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።

፲፬፤ እንዲሁም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን፡ ሕጹጽ ፡ የሚያደርጉትን ፤ ከአብ ፡ ያይደለ ፡ ከሌላ ፡ አካል ፡ ተገኘ፡ የሚሉትን ፡ እርሱም ፡ ፍጹም ፡ ጸጋውን ፡ ይነሣቸዋል ።

፲፭፤ እኛ ፡ ግን ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ በመለኮት ፡ አንድነት፡ የተካከሉ ፤ በሦስት ፡ አካላት ፡ ፍጹማን ፡እንደሆኑ ፡ እንዲህ ፡ እናምናለን ፡ እንዚህም ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ፡አብ እንዱ ፡ ቅዱስ ፡ ወልድ ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ፤ ከዓለም ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡ ዓለምን ፡ አሳልፈው ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ፤ አሜን ፤ በእውነት ።

### ምዕራፍ ፡ ፳፫ ። ክፍል ፡ ፪ ።

፩፤ ዳግመኛም ፡ ይህ ፡የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ የተመሰገነ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ፡ የጻፈውን፡ መልእክት፡ በተረጐመበት፡ አንቀጽ፡ ይህን፡ተናገረ ፤ ይኸውም ፡ ከትርጓሜው፡ ሰባተኛ ፡ አንቀጽ፡ነው

፪፤ የተዋሐደውን ፡ ሥጋ ፡ ከመላእክት ፡ ባሕርይ ፡ የነሣው ፡ አይደለም ፡ ከአብርሃም ፡ ባሕርይ፡ ነሣው፡ እንጂ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።

፫፤ ለዚህ ፡ ታላቅ ፡ ፍቅር ፡ አንክሮ ፡ ይገባል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ወገን ፡ ለተደረገ ፤ ለማይመረመር ፡ ለዚህ ፡ ፍቅር ፡ አንክሮ ፡ ይገባል፡ ይህ ፡ ለመላእክት ፡ ያላደረገው ፡ ነው ።

## ዘዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ም ፡ ፴፯ ፡

፴ ፤ ወባሕቱ ፡ እኩሥት ፡ ግብረ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነሥአ ፡ እምህላዌነ ፡ ፍጹመ ፡ ትስብእተ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ወልቡና ፡ ዘፍጹም ፡ በአካሉ ፡ ወቦቱ ፡ ተዋሐደ ፡ ቃል ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንብል ከመ ፡ ውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ።

፴፩ ፤ ወዳእሙ ፡ እመ፡ ንቤ ፡ እስመ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘበአማን ፡ ዓዲመ ፡ ንሕነ ነእምር ፡ ጽምረቶ ፡ ምስለ ፡ ቃል ፡ ለዘውእቱ ፡ እምኔነ ፡ በተዋሕዶ ፡ ዘኢይትነገር ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወበከመ ፡ ኢያፍለሰ ፡ ሥጋ ፡ ህላዌሁ ፡ ለመለኮት ፡ ከማሁ ፡ መለኮትሂ ፡ ኢያፍለሰ ፡ ህላዌሁ ፡ ለሥጋ፡ ውእቱ ፡ ወልድ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ኅቡረ ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፴፪ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናነክር ፡ ከመዝ ፡ ሶበ ፡ ንሰምዕ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንበሮ ፡ ለባሕቲቱ ለዘውእቱ ፡ እምኔነ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ መላእክት ፡ ዝንቱ ፡ ዘረሰዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልዕልተ ፡ ኵሉ ኅይላት ፡ ሰማያውያን ።

፴፫ ፤ ይቤ ፡ ወእምኵሉ ፡ ስም ፡ ዘይሰመይ ፡ አኮ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ በዘይመጽእኒ ፡ ዓለም ፡ እስመ ፡ ቦሙ ፡ ስም ፡ ለኃይላት ፡ እለ ፡ ኢናእምሮሙ ፡ ወኢንጤይቆሙ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፶፩ና ፡ ፶፪ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፬ ።

፴፬ ፤ ይቤ ፡ ወኵሎ ፡ እግረረ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወኢረሰዮ ፡ ከመዝ ፡ መልዕልቴሆሙ ፡ ባሕቲቱ ፡ ከመ ፡ ዘያከብሮ ፡ ወባሕቱ ፡ እመሰ ፡ ይደሉ ። አስተማስሎቱ ፡ ይመስል ፡ እግዚአ ፡ ላዕለ ፡ አግብርቲሁ ። መዝ ፡ ፰ ፡ ፮ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፯ ።

፴፭ ፤ ሚመጠን ፡ ዝንቱ ፡ ፍርሃት ፡ ዓቢይ ፡ ዘዝንቱ ፡ ግብር ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ኅይላተ ፡ ሰማይ ፡ ኮንዎ ፡ አግብርተ ፡ ለዘውእቱ ፡ እምኔነ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፩ደ ፡ ምስሌሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ። መዝ ፡ ፺፯ ፡ (፺፯) ፡ ፯ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

፴፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሀሊ ፡ ወይክል ፡ ይንሣእ ፡ ፩ደ፡ ዘየዐቢ ፡ እምኵሉ ፡ ኅይላት ፡ ወዳዕሙ ፡ ኢይሬስዮሙ ፡ ይትአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ አግብርት ፡ አላ ፡ ያከብርዎ ፡ በእንተ ፡ ትሩፋት ። ይሁ ፡ ፩ ፡ ፱።

፴፯ ፤ ወአኮ ፡ በዝየ ፡ ዘከመዝ ፡ አላ ፡ ረሰየ ፡ ኵሎ ፡ ይግነይ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወኢረሰዮሙ ፡ ይግነዩ ፡ ሎቱ ፡ ከመዝ ፡ ከመ ፡ አላ ፡ ግናይ ፡ ዘእልቦ ፡ ካልዕ ፡ ዘከማሁ ። ዕብ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ። ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፰—፲፬ ።

## ዘዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ም ፡ ፴፯ ።

፴ ፤ ተዋሕዶንም ፡ እስረዳለሁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል በአካሉ ፡ ፍጹም ፡ የሚሆን ፤ ነፍስ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሥጋን ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ ነሥቷልና ፡ እርሱንም ፡ ተዋሕዶአልና ፡ ስለዚህም ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደሆነ ፡ እንናገራለን ።

፴፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እውነተኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ ብንናገር ፤ ወዲህም ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ የተገኘ ፡ ሥጋ ፡ ያለመለየት ፡ በማይመረመር ፡ ተዋሕዶ ፡ ከቃል ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ መሆኑን ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ፤ ሥጋ ፡ የመለኮትን ፡ ባሕርይ ፡ እንዳለወጠ ፡ መለኮትም ፡ እንዲሁ ፡ የሥጋን ፡ ባሕርይ ፡ አልለወጠም ፤ እርሱ ፡ ወልድ ፡ በተዋሕዶ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ ነው ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፴፪ ፤ ስለዚህ ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ የተገኘ ፡ ሥጋን ፡ ብቻ ከመላእክት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ በዕሪናው ፡ እንደ ፡ አስቀመጠው ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ እናደንቃለን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰማይ ፡ ካሉ ፡ መላእክት ፡ ሁሉ ፡ በላይ፡ ያደረገው ፡ ይህ ፡ ነው ።

፴፫ ፤ ከሚጠራ ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ አደረገው ፡ አለ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለማናውቃቸው ፤ ለማንረዳቸው ፡ ለመላእክት ፡ ስም ፡ አላቸውና ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፶፩ና ፡ ፶፪ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፬ ።

፴፬ ፤ ሁሉን ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ አድርጎ ፡ አስገዛለት ፡ አለ ፡ እንደሚያከብረው ፡ አድርጎ ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ከነርሱ ፡ በላይ ፡ ያደረገው ፡ አይደለም ፡ መመሰል ፡ አይገባም ፡ እንጂ ፡ የሚገባ ፡ ከሆነስ ፡ ከባሮቹ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ጌታን ፡ ይመስላል ። መዝ ፡ ፰ ፡ ፮ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፯ ።

፴፭ ፤ የዚህ ፡ ተዋሕዶ ፡ መመርመሩ ፡ ምንኛ ፡ ያስፈራልን? እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ስለሆነ ፡ ከእኛ ፡ ለተገኘ ፡ ሥጋ ፡ መላእክት ፡ ተገዥዎች ፡ ሆነውታልና ። መዝ ፡ ፺፯ ፡ (፺፯) ፡ ፯ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

፴፮ ፤ እግዚአብሔርስ ፡ ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ የሚችል ፡ ነው ፡ ከመላእክት ፡ ሁሉ ፡ አንዱን ፡ በላይ ፡ አድርጎ መሾም ፡ ይቻለዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ባሮች ፡ እንዲታዘዙለት ፡ አያደርጋቸውም ፡ ስለትሩፋቱ ፡ ያከብሩታል ፡ እንጂ ። ይሁ ፡ ፩ ፡ ፱ ።

፴፯ ፤ በዚህ ፡ በሥጋ ፡ አምላክነት ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ ሁሉን ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ እንዲገዛለት ፡ አደረገ ፡ እንጂ ፡ መላእክት ፡ ለአለቃቸው ፡ እንደሚገዙለት ፡ ያለ ፡ አገዛዝ ፡ እንዲገዙለት ፡ ፈጽሞ አላደረገም ፡ እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሌለው ፡ አገዛዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ዕብ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ። ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፰—፲፬ ።

## ዘቄርሎስ ፡ ም ፡ ፹፫ ።

፲ ፤ ከመዝ ፡ ነአምን ፡ በ፩ዱ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ ወአኮ ፡ ንሕነ ፡ ከመ ፡ ዘይሰግድ ፡ ለብእሲ ፡ ወለቃል፤ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ምትሐተ ፡ ወጽላሎተ ፡ በፍልጠት ፡ ዘይበውእ ፡ ኅቡረ ፡ ወዘይረስይዎሙ ፡ ፪ተ ፡ አላ ፡ ንሰግድ ፡ ለ፩ዱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወሥጋሂ ፡ ኢኮነ ፡ ነኪረ ፡ እምነ ፡ ቃል ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ምስሌሁ ፡ ለግሙራ ።

### ክ ፍ ል ፲፪ ።

፲፩ ፤ እምድርሳነ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ ንተሉ ፡ ሕሊና ፡ ርትዕተ ፡ ወንትመየጥ ፡ ኀበ ፡ነገረ ፡ ጽድቅ ፡ ወኢንብል ፡ ነኪር ፡ ውእቱ ፡ መለኮት ፡እምነ ሕማም ፡ ከመ ፡ በዝንቱ ፡ ኢንብል ፡ እምቅድመዝ ፡ እስመ ፡ ልደት ፡ ሥጋዊ ፡ አኮ ፡ ልደቱ ፡ ወኢንብል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ለካልዕ ።

፲፪ ፤ ወኢንከሕድ ፡ ዘኮነ ፡ ዲበ ፡ ህላዌ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ ይትወደይ ፡ ሐፂን ፡ ውስተ ፡ ላህበ ፡ እሳት ፡ ወይትዌከፍ ፡ ላህበ ፡ እሳት ፡ በተዋሕዶቱ ፡ ምስሌሁ ፡ እስመ ፡ ሶበ ፡ ይዘበጥ ፡ ሐፂን ፡ ዘምስለ ፡ እሳት ፡ ኅቡረ ፡ ይትዌከፍ ፡ ዝብጠተ ፡ ወኢይትዔመፅ ፡ ህላዌ ፡ እሳት ፡ በምንትኒ ፡ እምነ ፡ ዝብጠት ፡ ከመዝ ፡ ንለቡ ፡ እስመ ፡ አማኑኤል፡ቃል፡ሐመ፡በሥጋ፡እንዘ፡ኢየሐምም፡በመለኮቱ ፡

፲፫ ፤ ይቤ ፡ ጸውዐኒ ፡ መፍቅድ ፡ እትወሐድ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ከመ ፡ እፍታሕ ፡ ማእሰረ ፡ ኃጢአት ፡ ወተሰቀልኩ ፡ እስመ ፡ ኮንኩ ፡ ሰብአ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ከመ ፡ አብጥል ፡ ኃጢአተ ፡ ኵሉ ፡ በሥጋየ ፡ወሞትኩ ፡ በከዊነ ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ።

፲፬ ፤ ወኢሞተ ፡ መለኮትየ ፡ አላ ፡ ጼወውኩ ፡ ሲኦለ ፡ ወተንሣእኩ ፡ በሥልጣነ ፡ ባሕቲትየ ፡ ነፋሕኩ ፡ በገጸ ፡ አርዳእየ ፡ አጠይቅ ፡ ከመ ፡ ፈጣሪ ፡ አነ ፡ ዘነፋሕኩ ፡ ውስተ ፡ ገጹ ፡ ለብእሲ ፡ ዘነበረ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ ዘውእቱ ፡ አዳም ። ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፪ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

፲፭ ፤ ወ፩ዱ ፡ ዘእምሥላሴ ፡ ውእቱ ፡ ዘተሰቅለ ፡ ወበሥጋ ፡ ዘተወከፈ ፡ ሞተ ፡ ዝንቱ ፡ ኮነ ፡ ፩ደ ፡ ምስሌሁ ፡ ወኢሞተ ፡ መለኮት ፡ ዘውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ምስለ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ኢይበሉ ፡ ካልአንሂ ፡ ተሰቅሉ ፡ ምስሌሁ ፡ እትናገር ፡ በእንተ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፲፮ ፤ ወለእመ ፡ ንቤ ፡ ከመ ፡ ቃል ፡ ተወከፈ ፡ ሕማመ ፡ በሥጋ ፡ ንሕነሰ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ተሰቅለ ፡ ወካልአንሰ ፡ ህላዌያት ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ኢሐሙ ።

## ዘቄርሎስ ፡ ም ፡ ፹፫ ።

፲ ፤ በአንድ ፡ የባሕርይ ፡ ገዥ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲህ ፡ እናምናለን ፤ ለሰውና ፡ ለቃል ፡ ለያይቶ ፡ እንደሚሰግድ ፡ ለያይተን ፡ የምንሰግድ ፡ አይደለም ፤ በመለያየት ፡ በሚገቡና ፡ ሁለት ፡ በሚያደርጓቸው ፡ በምትሐት ፡ በምሳሌ ፡ እንዳይሆን ፤ ለአንዱ ፡ ለእርሱ ፡ ብቻ ፡ እንሰግዳለን ፡ እንጂ ፤ ሥጋም ፡ ከቃል ፡ ልዩ ፡ አይደለም ፤ ፈጽሞ ፡ ከቃል ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

### ክ ፍ ል ፲፪ ።

፲፩ ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ከተናገረው ፡ ድርሳን ፡ እናመጣለን ፤ እኛስ ፡ የቀናች ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡እንናገራለን ፤ እውነት ፡ ነገርንም ፡ ወደ ፡ መናገር ፡ እንመለሳለን ፡ አለ ፤ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ልደት ፡ ሥጋዊ ፤ ገንዘቡ ፡ አልነበረምና ፡ ታመመ ፡ የማንል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሌላ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ እንደማንልም ፤ መለኮት ፡ ከሕማም ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ አንልም ።

፲፪ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በረቂቅ ፡ ባሕርይ ፡ የሆነውን ፡ ተዋሕዶ ፡ አንካድ ፡ ብረት ፡ ከእሳት ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ ከእሳትም ፡ በመዋሐዱ ፡ የእሳትን ፡ ባሕርይ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያደርግ ፤ ብረት ፡ በመዶሻ ፡ በተመታ ፡ ጊዜ ፡ ከእሳት ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ እንደሚመታ ፡ ግን ፡ ከመዶሻው ፡ የተነሣ ፡ የእሳት ፡ ባሕርይ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ እንዳይጐዳ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ በመለኮቱ ፡ ሕማም ፡ ሳይኖርበት ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፡ እንዲህ ፡ እናስተውል ።

፲፫ ፤ ፈቃድ ፤ ሥጋን ፡ እንድዋሐድ ፡ አደረገኝ ፡ የኃጢአትን ፡ ፍዳ ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፤ መከራም ፡ ተቀበልኩ ፡ በሥጋዬ ፡ የሁሉን ፡ ኃጢአት ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ሰው ፡ ሆኛለሁና ፡ ሁለተኛ ፡ አዳም ፡ ሆኜ ፡ ሞትኩ ።

፲፬ ፤ መለኮቴ ፡ አልሞተም ፡ ሲኦልን ፡ በዘበዝኩ ፡እንጂ ፤ በገዛ ፡ ሥልጣኔም ፡ ተነሣሁ ፡ እንጂ ፤ በገነት ፡ በነበረ ፡ ሰው ፡ በአዳም ፡ በንፍሐት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ያሳደርኹ ፡ ፈጣሪ ፡ እኔ ፡ መሆኔን ፡ አስረዳ ፡ ዘንድ ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ፊት ፡ እፍ ፡ ብዬ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳደርኩ ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፪ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

፲፭ ፤ የተሰቀለው ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ነው ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ይህ ፡ቃል ፡ በተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ሞተ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ መለኮት ፡ ግን ፡ አልሞተም ፡ በአካል ፡ ልዩ ፡ የሚሆኑ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተሰቀሉ ፡ እንዳይሉ፡የአብ፡የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ነገር፡ እናገራለሁ ።

፲፮ ፤ ቃል ፡ በሥጋ ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ብንናገርም ፤ እኛ ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፤ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ እናምናለን ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ ሁለቱ፡አብ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡መከራ፡አልተቀበሉም ።

ዘቄርሎስ ፡ ም ፡ ፸፩ ።

ክፍል ፡ ፳፫ ።

፺፩ እምነ ፡ መልእክት ፡ ዘእምኀበ ፡ ዝንቱ ፡ መምህር፡ ኀበ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ፩ዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፪ተ ፡ ወለእመኒ ፡ ይትዐወቅ ፡ እም፪ቱ ፡ በኢ.ቱሳሔ ፡ እብእ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ህላዌ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ በእምጣነ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ አኮ ፡ ውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ እም፪ቱ ።

ክፍል ፡ ፳፬ ።

፺፪ ፤ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ መምህር ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ምሥራቅ ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ ወ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ውእቱ ፡ ምስሌነ ፡ በትስብእቱ ወተዋሕዶቱሂ ፡ እም፪ቱ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ፩ዱ፡ እግዚእ ፡ ውእቱ ፡ ዘነአምን ፡ ቦቱ ፡ ወ፩ዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘከመ ፡ እምነት ፡ ተዋሕዶ ፡ በኢ.ቱሳሔ ፡ ወነአምን ፡ በድንግል ፡ ንጽሕት ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ወላዲተ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፤ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወረሰዮ ፡ ለሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ ፩ደ ፡ ምስሌሁ ፡ እምአመ ፡ ጊዜ ፡ ተፀንሰ ፡ ቦቱ ።

ክፍል ፡ ፳፭ ።

፺፫ ፤ እምሥጢረ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘዝንቱ ፡ ሊቅ ፡ በካልእ ፡ ዓመት ፡ እምዕዋድ ፡ በከመ ፡ እቤ ፡ ቅድመ ፡ ህላዌሁ ፡ ለሰብእ ፡ ኮነ ፡ ለሞት ፡ ወለሙስና ፡ በዓሊ.ዎቱ ፡ ለአዳም ።

፺፬ ፤ ወፈቀደ ፡ ፈጣሪ ፡ ይፍጥሮ ፡ ዳግመ ፡ ዘከመ ፡ ሀልዎቱ ፡ ቅድመ ፡ ወይክሥቶ ፡ በኢ.ሙስና ፡ ወኢ.ርስሐት ፡ በዓይ ፡ አምሳል ፡ ይደሉ ፡ ይኩን ፡ ዝንቱ፡ በእንተ ፡ ቃል ፡ ማሕየዊ ፡ ዙሉ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ያጽንዖ ፡ ለሰብእ ፡ መዝ ፡ ፺፬ (፺፫)፴ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።

፺፭ ፤ ነጽር ፡ እንከ ፡ በልቡና ፡ እስመ ፡ ኀይለ ፡ ምሥጢር ፡ ዙለንታሁ ፡ ለዝንቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ እንዘ ፡ ሕይወት ፡ ወማሕየዊ ፡ ውእቱ ከመ ፡ በኀይል ፡ ዘኢ.ይትነገር ፡ ያርኢ. ፡ ሥጋሁ ፡ መዋኤ ፡ ሞት ፡ ወሙስና ፡ ውእቱ ፡ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፳፪። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

፺፮ ፤ ወኢ.ንበል ፡ በአይ ፡ አምሳል ፡ ወበአይ ፡ አርአያ ፡ ዘከመ ፡ ሐፂን ፡ አመ ፡ ይትወደይ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ይገድፍ ፡ እሳት ፡ ላህበ ፡ ዚአሁ ፡ ወግብሮ ፡ ውስቴቱ ወበዝንቱ ፡ ይሬስዮ ፡ እሳተ ፡ ወይሁብ ፡ ኀይለ ፡ እሳት ።

